# ስለ ጥናቱ መረጃ

[ኖሳል ኢንስቲትዩት ፎር ግሎባል ሔልዝ* ፤ ሜልበርን ዩኒቨርስቲ]

**ፕሮጀክት፡ እንደምን አሉ?**

THE UNIVERSITY OF MELBOURNE

ፕሮፌሰር ባርባራ ማክፔክ (ኃላፊ ተመራማሪ)
ስልክ ቁጥር፡ +61 3 83449299 ኢ ሜይል፡ ni-info@unimelb.edu.au

## መግቢያ

በዚህ ጥናት ለመሳተፍ ፍላጎት በማሳየትዎ አመሰግናለሁ፡፡ ከዚህ በመቀጠል ያሉት መረጃዎች ስለ ጥናቱ ተጨማሪ መረጃ እንዲኖርዎ የተዘጋጁ ሲሆን እርስዎ በጥናቱ ለመሳተፍ ለሚያደርጉት ውሳኔ ይረዱዎታል፡፡

እባክዎን በቂ ጊዜ በመውሰድ ከዚህ ቀጥሎ ያሉትን መረጃዎች በጥንቃቄ ያንብቡ፡፡ ስላልገባዎት ነገር ወይም ተጨማሪ መረጃ ስላስፈለግዎት ነገር ጥያቄ መጠየቅ ይችላሉ፡፡

በዚህ ጥናት ላይ የሚሳተፉት ፈቃደኛ ከሆኑ ብቻ ነው፡፡ መሳተፍ የማይፈልጉ ከሆነ አለመሳተፍ ይችላሉ፡፡ ጥናቱ ላይ መሳተፍ ከጀመሩ በኋላም ማቋረጥ ከፈለጉም በፈለጉት ጊዜ ማቋረጥ ይችላሉ፡፡

## ጥናቱ ስለምንድን ነው?

የዚህ ጥናት ፕሮጀክት ዋና ዓላማ የ COVID-19 ወረርሽኝ በዓለም አቀፍ ደረጃ በግለሰቦችና በቤተሰብ ኢኮኖሚ እና ጤና ላይ የሚያመጣውን ተፅዕኖ መዳሰስ ነው፡፡ ጥናቱ የወረርሽኙ ተፅዕኖ ምን ያህል እንደሆነ ፤ ተፅዕኖው በተለያዩ ሀገራት በሚኖሩ ግለሰቦች መካካል ምን ያህል እንደሚለያይ (ለምሳሌ በማህበራዊ በኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች እና በጊዜ ዑደት) ለማወቅ ነው፡፡ ጥናቱ ሜልበርን ዩኒቨርስቲ በሚገኙት በኖሳል ኢንስቲትዩት (Nossal Institute) እና በስኩል ኦፍ ፖፑሌሽን ኤንድ ግሎባል ሔልዝ (School of Population and Global Health) ገንዘብ ድጋፍ የሚካሄድ ነው፡፡

## በዚህ ጥናት ላይ ምን እንዳደርግ ነው የምጠየቀው?

በዚህ የጥናት ዳሰሳ ላይ ለመሳተፍ ከተስማሙ ስለራስዎ የጤና ሁኔታ ፣ የኢኮኖሚ ሁኔታ እና መሰረታዊ የሆኑ ዋና ዋና መረጃዎችን የሚዳስሱ ጥያቄዎችን ይጠየቃሉ፡፡ ቃለ መጠይቁን መሙላት በአማካይ ከ 30 እስከ 45 ደቂቃ ሊወስድ ይችላል፡፡

ሌላ ግለሰብ በጥናቱ ላይ ለመሳተፍ ያለ ምንም አይነት ጫና ፈቃደኛ ከሆኑ እና እርስዎን ከወከሉ ፣ እርስዎ ግለሰቡን/ቧን በመወከል ቃለ መጠይቁን መሙላት ይችላሉ፡፡ ጥያቄዎቹን ለመመለስ ለወከሉዎት ግለሰብ ይህንን የጥናት መረጃ እንዲያነቡላቸውና ግለሰቡ/ቧ በጥናቱ ላይ ለመሳተፍ ፈቃደኛ መሆናቸውን እንዲጠይቁ አበክረን እናሳስብዎታለን፡፡

ይህ ጥናት የእርስዎ ነባራዊ ሁኔታዎች በጊዜ ዑደት እንዴት እንደሚቀየሩ መረጃዎችን ለማግኘት ያለመ ነው፡፡ የኢሜይል አድራሻዎን ካጋሩን ፣ ሌሎች የዚህ ጥናት አካል ከሆኑ በየሦስት ወሩ እስከ ታህሳስ 22 ፣ 2014 ዓ.ም. የሚደረጉ ቀጣይ ጥናቶች ላይ እንዲሳተፉ ጥሪ ልናደርግልዎ እንችላለን፡፡ በተጨማሪም በዚህኛው (በአሁኑ) ጥናት ላይ ከእኛ ጥሪ ሳይደረግልዎት በተደጋጋሚ እስከፈለጉት ጊዜ መሳተፍ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን በዚህኛው ጥናት ላይ አሁንም ይሁን ወደፊት ለመሳተፍ የኢሜይል አድራሻዎን የመስጠት ግዴታ የለብዎትም፡፡

## እዚህ ጥናት ላይ መሳተፍ ሊያስገኝ የሚችለው ጥቅም ምንድን ነው?

እዚህ ጥናት ላይ በመሳተፍዎ በቀጥታ ተጠቃሚ ይሆናሉ ብለን ቃል መግባት ያዳግተናል ፤ ለተሳትፎዎ የምናበረክትልዎት ክፍያ ወይም ማካካሻም የለም፡፡ ነገር ግን እርስዎ የሚሰጡት መረጃ ወደፊት የ COVID-19 ወረርሽኝ ያስከተላቸውን ተፅዕኖዎች ለመቀልበስ የሚደረጉ ውጤታማ የፖሊሲ እርምጃዎች እንዲኖሩ ያስችላል፡፡

## እዚህ ጥናት ላይ መሳተፍ ሊያስከትል የሚችለው ጉዳት ምንድን ነው?

በዚህ ጥናት ላይ ከመሳተፍ ጋር ተያይዞ ሊመጣ የሚችል ጉዳት ቢኖር ምናልባት የመረጃ ሚስጥራዊነት መባከን ነው (ለምሳሌ እርስዎ የኢሜይል አድራሻዎን ቢሰጡንና ቃለ መጠይቁ የሚደረግበት ድህረ ገጽ ቢበረበር ወይም ሃክ ቢደረግ)፡፡ የእርስዎ ግላዊ መለያ ፤ ለቃለ መጠይቁ የሚመልሷቸው መልሶች ከሌሎች መረጃዎች ጋር በመሆን በሜልበርን ዩኒቨርስቲ በሚገኝ ጥብቅ በሆነ የመረጃ ቋት (ሰርቨር) ውስጥ ይከማቻሉ፡፡ በተጨማሪም ከእርስዎ የሚገኘው መረጃ ከማን እንደተገኘ በማይታወቅ መልኩ ይቀመጣል (የእርስዎን ማንነት ለመለየት የሚያስችሉ መረጃዎች ለምሳሌ የኢሜይል አድራሻ የመሳሰሉት መረጃዎች በቋቱ ውስጥ ከሚከማቸው መረጃ ላይ ይነጠላሉ)፡፡ በተጨማሪም የዚህ ጥናት ውጤቶች የሚጠናቀሩት በማህበረሰብ ወይም በሀገር ደረጃ ነው እንጂ በግለሰብ ደረጃ አይደለም፡፡ በዚህ ጥናት ላይ እጅግ በጣም በርካታ ግለሰቦች ይሳተፋሉ ተብሎ ስለሚጠበቅ እርስዎን የተመለከቱ መረጃዎችን በመንግስት ወይም በዓለም አቀፍ ድርጅቶች ነቅሶ የማውጣት ዕድል በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ ነገር ግን ከመሳተፍዎ በፊት እነዚህን ነገሮች ያገናዝቡ፡፡

በተጨማሪም የ COVID-19 ወረርሽኝ በማህበራዊ ፣ በጤና ፣ እና በኢኮኖሚ ላይ የሚያስከትለውን ተፅዕኖ የሚዳስሱትን ጥያቄዎች በመመለስዎ የሀዘን እና የመረበሽ ስሜት ሊሰማዎት ይችላል፡፡ እንደዚያ አይነት ስሜቶች ካጋጠመዎት በአካባቢዎ የሚገኙ የማህበረሰብ ወይም የመንግስት ድጋፍ ሰጭ ማዕከላትን እንዲጎበኙ እንመክርዎታለን፡፡ ምናልባትም መሰል አገልግሎቶችን በስልክ ጥሪ ማዕከላት ሊያገኙ ይችላሉ፡፡

## የግዴታ መሳተፍ አለብኝ?

በጥናቱ ላይ የግድ መሳተፍ የለብዎትም፡፡ በዚህ ጥናት ላይ የመሳተፍ ወይም ያለመሳተፍ ውሳኔ በእርስዎ ሙሉ ፈቃድ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በፈለጉት ሰዓት ለጥናቱ ተመራማሪ ፕሮፌሰር ባርባራ ማክፔክ  ከታች በተጠቀሰው አድራሻ ኢሜይል በመላክ ጥናቱን ማቋረጥ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ከእርስዎ የተገኙትን መረጃዎች እርስዎ እስከመጨረሻው/እስከወዲያኛው በጥናቱ ላለመሳተፍ መወሰንዎን እስኪያሳውቁን ድረስ እናስቀምጣቸዋለን፡፡ ይህ የሚሆንበት ምክንያትም በ COVID-19 የሚመጡት ተፅዕኖዎች ለብዙ አመታት ሊቆዩ ስለሚችሉ እና አሁን ከተከሰተው ወረርሽኝ የሚገኘው ልምድ ወደፊት ሊመጡ በሚችሉ ተመሳሳይ ክስተቶች ላይ የሚደረጉ ውሳኔዎችን ስለሚያግዝ ነው፡፡ ያለንን የህግ አግባብነት እና የቁጥጥር ሥርዓት በመከተል ከእርስዎ የሚገኙትን መረጃዎችን እናስቀምጣለን፡፡ ከእርስዎ የተገኙትን መረጃዎች መረጃውን እርስዎ እንደሰጡ በማይታወቅበት መልክ (መረጃዎቹ ከእርስዎ እንደተገኙ በማይደረስበት መልክ) ለሌሎች በህግ ለተፈቀደላቸው እና መረጃውን ለጥናት ወይም ለሕዝብ ጥቅም ዓላማዎች ለሚያውሉ አካላት ልናጋራ እንችላለን፡፡

## ከዚህ ጥናት ፕሮጀክት የሚገኘው ውጤት ይነገረኛልን?

የኦንላይን ዳሰሳውን (ጥያቄዎቹን) ካጠናቀቁ በኋላ የተመረጡ የጥናቱ ውጤቶችን በሠንጠረዥ እና በቻርት መልክ እዚሁ ድህረ ገጽ ላይ ያገኙዋቸዋል፡፡ በተጨማሪም ከዚህ ጥናት በሚገኙ መረጃዎች መሠረት የሚዘጋጁ ጽሑፎች በሳይንሳዊ መጽሔቶች (ጆርናሎች) ላይ ይታተማሉ ፣ በተለያዩ የባለሙያዎች ኮንፈረንሶች ላይ ይቀርባሉ ፣ በፖሊሲ ውጥን መልክ ይዘጋጃሉ ፤ በመጽሔቶች ወይም የመረጃ አውታሮች ላይ በሙያዊ ምልከታ መልክ ይቀርባሉ፡፡ ወደ ተጠቀሱት የሕትመት መዳረሻዎች የሚመሩ አገናኞች (ሊንኮችም) ወደፊት እዚሁ ድህረ ገፅ ላይ ይቀመጣሉ፡፡

## ከእኔ የሚገኙ መረጃዎች ምን ይደረጋሉ?

ከእርስዎ የሚገኙትን መረጃዎች ወሰን ለሌለው ጊዜ እናስቀምጣለን፡፡ ይህ የሚሆንበት ምክንያትም በ COVID-19 የሚመጡት ተፅዕኖዎች ለብዙ አመታት ሊቆዩ ስለሚችሉ እና አሁን ከተከሰተው ወረርሽኝ የሚገኘው ልምድ ወደፊት ሊመጡ በሚችሉ ተመሳሳይ ክስተቶች ላይ የሚደረጉ ውሳኔዎችን ስለሚያግዝ ነው፡፡ ያለንን የህግ አግባብነት እና የቁጥጥር ሥርዓት በመከተል ከእርስዎ የሚገኙትን መረጃዎችን እናስቀምጣለን፡፡ ከእርስዎ የተገኙትን መረጃዎች መረጃውን እርስዎ እንደሰጡ በማይታወቅበት መልክ (መረጃዎቹ ከእርስዎ እንደተገኙ በማይደረስበት መልክ) ለሌሎች በህግ ለተፈቀደላቸው እና መረጃውን ለጥናት ወይም ለሕዝብ ጥቅም ዓላማዎች ለሚያውሉ አካላት ልናጋራ እንችላለን፡፡

የጥናቱን ተሳታፊዎች ማንነት እንዳይታወቅ ለማስቻል እርስዎ ለቃለ መጠይቁ የሚመልሷቸው መልሶች መረጃው ከማን እንደተገኘ በማይታወቅበት መልኩ (የእርስዎን ማንነት ለመለየት የሚያስችሉ መረጃዎች ለምሳሌ የኢሜይል አድራሻ የመሳሰሉት መረጃዎች በቋቱ ውስጥ ከሚከማቸው መረጃ ላይ ይነጠላሉ) በሜልበርን ዩኒቨርስቲ በሚገኝ ጥብቅ በሆነ የመረጃ ቋት (ሰርቨር) ውስጥ ይከማቹና በኖሳል ኢንስቲትዩት ባለሞያዎች ይተዳደራሉ፡፡

## ተጨማሪ መረጃ ከየት ማግኘት እችላለሁ?

ስለዚህ ጥናት ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ከፈለጉ የጥናቱን ኃላፊ ተመራማሪ ፕሮፌሰር ባርባራ ማክፔክን ማግኘት ይችላሉ (ስልክ ቁጥር፡ +61 3 83449299 ኢ-ሜይል፡ ni-info@unimelb.edu.au)፡፡

## ስለጥናቱ የተለየ ጥያቄ ካለኝ ማንን ማነጋገር እችላለሁ?

ይህ የጥናት ፕሮጀክት በሜልበርን ዩኒቨርስቲ የጥናት ሥነ ምግባር ኮሚቴ (Human Research Ethics Committee) ፈቃድ ተሰጥቶታል፡፡ ስለ ጥናቱ አፈፃፀም ቅሬታ ወይም ስጋት ካለዎት እና ያንን ስጋት ከጥናት ቡድኑ ጋር መወያየት ካልፈለጉ የሜልበርን ዩኒቨርስቲ የጥናት ሥነ ምግባር ኮሚቴ ኃላፊን ቀጥሎ በተጠቀሰው አድራሻ ማነጋገር ይችላሉ (ስልክ ቁጥር፡ +61 3 8344 2073 ኢ-ሜይል፡ HumanEthics-complaints@unimelb.edu.au). የሚቀርቡ ቅሬታዎች በሙሉ በሚስጥር ይያዛሉ፡፡ ቅሬታዎን በሚያቀርቡበት መልዕክት እባክዎትን የጥናቱን ቡድን ወይም የጥናቱን ስም ወይም የጥናቱን የስነምግባር መለያ ቁጥር ይጥቀሱ፡፡

* *ኖሳል ኢንስቲትዩት ፎር ግሎባል ሔልዝ* የሚገኘው በሜልበርን ዩኒቨርስቲ ስኩል ኦፍ ፖፑሌሽን ኤንድ ግሎባል ሔልዝ ውስጥ ነው፡፡ ኖሳል ኢንስቲትዩት ፎር ግሎባል ሔልዝ (https://mspgh.unimelb.edu.au/centres-institutes/nossal-institute-for-global-health/about-us/about-the-nossal-institute) ሰር ጉስታቭ ኖሳል የህክምና ጥናት ለሰዎች ጤና መሻሻል እንዲውል ላበረከቱት አስተዋፅኦ ለክብራቸው ይሆን ዘንድ በስማቸው የተሰየመ ነው፡፡ ኢንስቲትዩቱ እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ2006 ዓ.ም. ተጋላጭ ለሆኑ ህብረተሰቦች ጤና ጥብቅና ተቋቋመ፡፡ የኢንስቲትዩቱ ተልዕኮ የጤና ስርዓቶችን ጥራት ፣ በዋጋ ተመጣጣኝነት እና አካታችነትን ተግባራዊ የሆኑ ምርምሮችን ፣ የተሞከሮና የልማት ምላሾችን መሠረት በማድረግ ማጠናከር ነው፡፡